# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## ከጥምቀት ገሃድ እስከ ቅበላ ጾም አስተርእዮ ይባላል።

ዘመነ አስተርእዮ የሚባለው ከጥር ፲፩ እስከ ጥር ፴ ቀን ድረስ ያሉት ዕለታትና ሳምንታት ናቸው። … በእነዚህ ዕለታትና ሳምንታት የሚዘመረው መዝሙር አንሰሰወ አስተርአየ ተወለደ ተጠመቀ ከብካብ ማይ መርዓዊ የሚሉ ይሆናሉ። ዘመነ አስተርእዮ የተባለበትም ምክንያት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ በእስራኤል አውራጃ እየዞረ በመምህርነት ስለተገለፀ አስተርእዮ ወይም በዓለ ኤጲፋንያ ተባለ። ይኸውም አስተርአየ (ተገለጠ) አስተርእዮ (መገለጥ) ማለት ሲሆን ኤጲፋንያ የሚለው ቃል ደግሞ ምስጢሩ ያው ሆኖ ቃሉ ግሪክኛ ነው።

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ሖረ ኢየሱስ በትፍሥሕት ውስተ ከብካብ
(ኢየሱስ በፍጹም ደስታ ወደ ሠርግ ቤት ሄደ)

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| ፩ | ዕብ ፪፤፩-፲፩ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| ፪ | ፩ኛ ዮሐ ፭፤፩-፲፫ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| ፫ | የሐዋ ሥራ ፲፤፴፬-፴፱ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### የዕለቱ ምስባክ

እስመ መምህር ሕግ ይሁብ በረከተ
ወየኀውር እምኃይል ውስተ ኃይል
ወያስተርኢ አምላከ አማልክት በጽዮን

የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣል
ከኃይል ወደ ኃይል ይሄዳል (ይሄዳሉ*)
ቅዱስ የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል።
መዝ ፹፫(፹፬)፤፯
*ይላል የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ

ትርጉም፥ ሕግን የሠራ ያስተማረ የወሰነ ጌታ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን ይሰጣል ታምራትን ከማድረግ ሌላውን ታምራት ወደ ማድረግ ይሄዳል። የሰው ልጅን የፈጠረ የአማልክት አምላክ ጌታ በኢየሩሳሌም ከድንግል በነሳው ሥጋ ተገለጠ ማለት ነው።

ወንጌል፥ ዮሐ ፪፤፩-፲፩
ቅዳሴ፥ እምቅድመ ዓለም (የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ)

## የዕለቱ ትምህርት

### የድንግል ማርያም አማላጅነት በቃና ዘገሊላ ሠርግ

ጋብቻ በሁሉ ዘንድ የከበረ መኝታውም ንጹሕ እንደሆነ ጌታ በሐዋርያው ጳውሎስ አድሮ እንዳስተማረ ሰዎችንም ከመጀመሪያው ይበዙ ይባዙ ምድርንም ይሞሏት ዘንድ በጋብቻ በረከት ባረከ (ዘፍ ፩፤፳፯-፳፰ ። ዕብ ፲፫፤፫-፯) ክቡር የሆነውን ጋብቻም በእርሱና በአማኞቹ መካከል ያለውን ግንኙነት በጋብቻ መስሎ ተናገረ (ሆሴዕ ፪፤፱-፲፰ ። ኤፌ ፭፤፳፭-ፍጻሜ)። መድኃኒታችንም ወደ ሠርጉ ቤት ድንግል ማርያምን የጠሩ ወዳጆቹ ሠርግ ቤት በመገኘት በጠላት ዲያቢሎስ በኤደን ገነት የተበላሸውን ሠርግ በመባረክና የጎደለውን በመሙላት የሥራው መጀመሪያ የሆነውን ተአምራቱን አደረገ። «ሠርግ አስደሳች ነገር ነው የወይን ጠጅ ደግሞ የልቦና ደስታ ነው» (መዝ ፩፻፫)። መድኃኒታችን ወደ ሠርግ ቤት ተጠራ፤ የዓለም ደስታ ወደ ደስታ ቦታ መጥቶ ሕይወት የወይን ጠጅ ወደሚቀዳበት ቤት ተጠራ፤ በቃና ዘገሊላ ለተደረገው ተአምር ምክንያት የሆነችው እርስዋ ናት በዘመን ሁሉ ነፍሳችንን የሚያነሳሳ ይህ አማላጅነትዋ ነው። የሠርጉ የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ ስለ እንግዶቹ ድንግል ማርያም አሰበች አሳዳሪው ማሰብ ያልቻለውን ነገር እርሷ አሰበች፤ በምህረቱ በመተማመን ወደ ልጅዋ ቀርባ የጠበቀ ልመና አሰማች (ዮሐ ፪፤፬) ልመናዋም ስለራሷ ሳይሆን በአማላጅነትዋ ልትጠቅማቸው ስላሰበችላቸው ሰዎች ነበር። መድኃኒታችንም «አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም» አላት። ምን ማለቱ ይሆን?

1) አንቺ ሴት ሲል መድኃኒታችን የስድብ ቃልን እንደሰነዘረ የሚገምቱ አልጠፉም፤ ነገሩ ግን ምስጢር እንጂ ስድብ አልነበረም። አዳም ከኤደን ገነት በተባረረበት ወቅት የሰማው የተስፋ ቃል «ከሴቲቱ የሚወለደው የእባቡን እራስ ይቀጠቅጣል» የሚል ነበር (ዘፍ ፫፤፲፭)፤ የተስፋው ጊዜም በተፈጸመ ጊዜ መሲሁ ከሴት ተወለደ «ወአመ በጽሐ ጊዜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልደ ወተወልደ እምብ እሴት» ብሎ ሐዋርያው እንደተናገረ (ገላ ፬፤፬)፤ በመስቀል ላይም የእባቡን ራስ መሲሁ ሲቀጠቅጥ የሴቲቱ ልጅ መሲሁም በእባቡ መርዝ እግሩ ሲነደፍ ትንቢቱ ሲፈጸም «አንቺ ሴት» በማለት ነበር የጠራት። በዚህ ሁሉ ሴት እያለ ሲጠራት፣ የተስፋውን ዘር ያስገኘች የሰዎች ሁሉ እናት መሆንዋን በሔዋን የተበላሸው የሰው ሁሉ ሕይወት የሚለወጥበት የሁለተኛው አዳም፣ ጠላትን የተበቀለው ወንድ ልጅ እናት መሆንዋን ለመግለጽ «አንቺ ሴት» አላት። ሴት ማለት ወንድ እንደሚለው ስም የጾታ ስም መለያ እንጂ የስድብ ቃል፤ የደካማነት ምልክት አይደለም። «እናትና አባትህን አክብር» ብሎ ሕግ የሰራ ጌታ (ዘጸ ፳) ቅድስት እናቱን አቃለለ ማለት ድንግልንና የድንግልን ልመና ከማቃለል አልፎ ጌታን መሳደብ ነው።

2) «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» በባሕሪይ መለኮቱ ተአዝዞ፤ አገብሮ የሌለበት ጌታ በሥጋ ታዛዥ ሆኖ ቢገለጥም የራሱ የሆነ የሥራ ጊዜ ነበረው። በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ እንደተዳፈልን «ጊዜ» እያለ ጌታ የሚናገረው የሞቱን የስቅለቱን ጊዜ ነበር። ድንግል ማርያምስ ለወይን ጠጅ ስትጠይቀው እርሱ ግን በዕለተ ዓርብ ስቴ ሕይወት፣ ስቴ መድኃኒት ሆኖ ስለሚፈሰው ደሙ ይናገር ነበር። ድንግል ስለሙሸራው ድግስና እንዲሁም የሙሽራው ጎደሎ የሚሞላበትን ሁኔታ ስትጠይቀው እርሱ ደግሞ በምክንያቱ አባቱ ስላዘጋጀው ሰማያዊ ሠርግና (የበጉ ሠርግ) የዓለምን ጎዶሎ ስለሚሞላው ደሙ ተናገረ። ጌታ በየአጋጣሚው «ጊዜዬ» በማለት ስለዕለተ ሞቱ መናገሩን በሚከተሉት ጥቅሶች ልብ እንበል (ዮሐ ፪፤፬ ። ዮሐ ፯፤፮ ። ዮሐ ፯፤፴ ። ዮሐ ፰፤፳ ። ዮሐ ፲፪፤፳፫-፳፯ ። ዮሐ ፲፫፤ ፩፥፲፮፥፴፪ ። ዮሐ ፲፯፤፩-፪ ። ማቴ ፳፮፤፲፰)። በጌቴሰማኒ የአባቱን ፈቃድ ያስቀደመ ጌታ (ሉቃ ፳፪፤፵፪) በቃና ዘገሊላ የእናቱን ጥያቄ መለሰ «በቃና መታዘዝ አሸነፈ» በቃና ዘገሊላ በድንግል ማርያም ፈቃድና አማላጅነት ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ለወጠ፤ በቀራንዮ ደግሞ በአባቱ ፈቃድ ደሙን የወይን ጠጅ አድርጎ አቀረበ፤ አብ በደብረ ታቦር የሚለውን እንሰማ ዘንድ «ውሎቱ ስምዕዎ - እርሱን ስሙት» እንዳለ ድንግልም የሚላችሁን አድርጉ በማለት የእናትነትዋን ምክር ገለጠች። መድኃኒታችን በቃና «አንቺ ሴት» ያላትን ድንግል እናቱን በመስቀል ላይም «አንቺ ሴት» በማለት ጠራት፤ ለመስቀል በኋላ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ በልጅዋ መስቀል ማህፀንነት የብዙዎች እናት ሆነች። አዲሱ ሰው አዳም የዳነው ሰው አባት ሲሆን አዲሲቱ ሔዋን ድንግል ማርያም ደግሞ የዳነው ሕዝብ እናት ሆናለች።

የእግዚአብሔር ሥራ በሁለተኛው አዳም እስከተገለጠበት ጊዜ ድረስ በነቢያት፣ በካህናተ-ኦሪት፣ በመሳፍንት፣ በአብርሃም፣ በይስሐቅ፣ በያዕቆብ፣ በሙሴ፣ በኢያሱ የተሰጠው የተገለጠው አገልግሎት ድኅነተ ነፍስን ያላመጣ ፍጹምነት የሌለው፣ ከመርገመ ኃጢአት የማያነጻ መናኛ የወይን ጠጅ ነበር። ማለፊያው የወይን ጠጅ ግን ከእውነተኛው የወይን ሐረግ ከክርስቶስ በክርስቶስ ተዘጋጀ። ሔዋን በድንግል ማርያም ተሻረች፤ አዳም በሁለተኛው አዳም ተተካ። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን «ወሐደግነ አበ ቀዳማየ ዘውእቱ አዳም ዘቦቱ ወሰነ» ማለትም «ለጥፋት የተጋለጥንበትን ቀዳማዊ አዳምን ተውን» አለች።

አገልጋዮች ሐዋርያትም በፈዘዙት የድንጋይ ጋኖች ውሃን (ቃሉን) ሙሉ፤ ጌታችንም በፈዘዙት የድንጋይ ጋኖች ውስጥ (በመርገመ አዳም በምክረ ሰይጣን) በተያዙት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣዕም ያለው ሕይወት እንዲኖር በከኃሊነቱ አደረገ። ጌትነቱም ለሁላችን ተገለጠ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ
EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM